በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኮልፌ ቀራኒዮ ክፈለ ከተማ

የ6ኛ ክፍል ሞዴል ፈተና

ሒሳብ ትምህርት 2018 ዓ.ም

የጥያቄ ብዛት፡ 30 የተፈቀደው ሰዓት:- 1 ስዓት

አጠቃላይ ትዕዛዝ

ይህ የሒሳብ ፈተና ነው፡፡ በዚህ ፈተና ውስጥ 30 ጥያቄዎች ተካተዋል። እያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ የሆነውን አማራጭ የያዘውን ፊደል በመምጥ ለመልስ መስጫ በተሰጠው ወረቀት ላይ በማጥቆር መልስ ይሰጣል፡፡ በፈተና ላይ የተሰጡትን ትዕዛዞች በጥንቃቄ በማንበብ ፈተናውን መስራት ይጠበቅባችኋል፡፡

መልስ የሚሰጠው ከፈተናው ጋር በተያያዘው የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ ነው፡፡ በመልስ መስጫው ላይ ትክክለኛው መልስ የሚጠቆረው በእርሳስ ብቻ ነው፡፡ ትክክለኛው መልስ በማጥቆር ሲሰራ ለማጥቆር የተፈቀደው ቦታ በሙሉ በሚታይ መልኩ በደንብ መጥቆር አለበት፡፡ የጠቆረውን መልስ መቀየር ቢፈለግ በፊት የጠቆረውን በደንብ በማጥፋት መፅዳት አለበት፡፡

ፈተናውን ሰርቶ ለመጨረስ የተፈቀደው ሰዓት 1 ሰዓት ነው፡፡ ፈተናውን ሰርቶ ለመጨረስ የተሰጠው ሰዓት ሲያበቃ ለመስሪያነት የተጠቀማችሁበትን እርሳስ ማስቀመጥ እና ፈተናውን መሰራት ማቆም አለባችሁ ፡፡

መኮረጅ ወይም በፈተና ሰዓት የፈተናን ህግ የማያከብር ተፈታኝ ፈተናው አይያዝለትም። ፈተናውን እንዳይፈተን ይደረጋል፡፡ ፈተናውን መስራት ከመጀመራችሁ በፊት በመልስ መስጫ ላይ መሞላት የሚገባውን መረጃ ሁሉ በጥንቃቄ መሞላት አለበት፡፡

LIVEWORKSHEETS

ፈተናው መስራት ጀምሩ ሳይባል መጀመር አይፈቀድም !

**ትዕዛዝ ፡ ለሚከተሉ ጥያቄዎች ከቀረቡላችሁ አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል ብቻ በመምረጥ በተዘጋጀው መልስ መስጫ ወረቀት ላይ አጥቁር(ሪ)**

1. ርዝመቱ 7 ሳ.ሜ እና ወረዱ 9 ሳ.ሜ የሆነ ሬክታንግል ስፋቱ ስንት ነው ?

   ሀ. 81 ሳ.ሜ$^2$ ሐ. 63 ሳ.ሜ$^2$

   ለ. 12 ሳ.ሜ$^2$ መ. 49 ሳ.ሜ$^2$

2. 1 ክ.ሜ$^2$ ስንት ሳ.ሜ$^2$ ይሆናል ?

   ሀ. 1,000 ሳ.ሜ$^2$ ሐ. 100 ሳ.ሜ$^2$

   ለ. 100,000 ሳ.ሜ$^2$ መ. 10,000 ሳ.ሜ$^2$

3. ርዝመቱ 5 ምድብ ወረዱ 4 ምድብ እና ከፍታው 2 ምድብ የሆነ የውሃ ታንከር ይዘት ስንት ነው?

   ሀ. 40 ኪዩቢክ ሐ. 25 ኩዩቢክ

   ለ. 11 ኪዩቢክ መ. 22 ኪዩቢክ

4. ከሚከተሉት ውስጥ 0.25 ሊትር ወደ ሳንቲ ሜትር ኩብ (ሳ.ሜ$^3$) ሲቀየር የቱ ነው ?

   ሀ. 25 ሳ.ሜ$^3$ ሐ. 2500 ሳ.ሜ$^3$

   ለ. 250 ሳ.ሜ$^3$ መ. 25,000 ሳ.ሜ$^3$

5. ከሚከተሉት አንዱ የህገኛ ክፍልፋይ ምሳሌ አይደለም ::

   ሀ. $\frac{7}{8}$ ሐ. $2\frac{3}{5}$

   ለ. $\frac{100}{300}$ መ. $\frac{85}{101}$

6. ከሚከተሉት መካከል የ $\frac{1}{5}$ አቻ ክፍልፋይ የሆነው የቱ ነው ?

   ሀ. $\frac{2}{10}$ ሐ. $\frac{4}{20}$

   ለ. $\frac{3}{15}$ መ. ሁሉም

LIVEWORKSHEETS

7. የ $2\frac{4}{5}$ ተገላቢጦሽ የትኛው ነው ?

ሀ. $\frac{14}{5}$ ሐ. $\frac{5}{14}$

ለ. $\frac{4}{10}$ መ. $\frac{8}{5}$

8. $6\frac{3}{8}$ ወደ ህገወጥ ክፍልፋይ ሲቀየር የቱ ነው ?

ሀ. $\frac{48}{8}$ ሐ. $\frac{51}{3}$

ለ. $\frac{51}{8}$ መ. $\frac{48}{3}$

9. የስሌት $2\frac{4}{5} \div 1\frac{3}{4}$ ውጤት ስንት ነው ?

ሀ. $\frac{2}{5}$ ሐ. $\frac{8}{5}$

ለ. $\frac{3}{4}$ መ. $\frac{88}{20}$

10. የ 125 እና 24.32 ልዩነት ስንት ነው ?

ሀ. 100.32 ሐ. 3040

ለ. 100.68 መ. 149.32

11.ከሚከተሉት መካከል $\frac{648}{10}$ ወደ አስርዮሻዊ ቁጥር ሲቀየር የቱ ነው?

ሀ. 0.648 ሐ. 6.48

ለ. 648 መ. 64.8

12. አንድ ሰው 7 ሰዓት ያህል ቢተኛ የቀኑን ስንት ሰዓት ተኝቷል ?

ሀ. $\frac{1}{2}$ ሐ. $\frac{1}{3}$

ለ. $\frac{7}{24}$ መ. $\frac{7}{12}$

13. 24 ቀናት የአንድ ወር ስንት መቶኛ ነው ?

ሀ. 85% ሐ. 75%

ለ. 80% መ. 60%

LIVEWORKSHEETS

14.በአንድ ት/ቤት ውስጥ የ6ኛ B ክፍል 26 ወንድ እና 24 ሴት ተማሪዎች ቢኖሩ የወንድ ተማሪዎች ቁጥር በመቶኛ ሲገለፅ ስንት ነው?

ሀ. 48%　　　　ሐ. 50%

ለ. 52%　　　　መ. 26%

15.ከሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች ውስጥ **ተጋማሽ ቁጥር የሚሆነው** የትኛው ነው ?

ሀ. 4263　　　　ሐ. 8979

ለ. 5978　　　　መ. 6701

16. ከሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች ውስጥ **ለ2 እና ለ3** ተካፋይ የሆነው የቱ ነው ?

ሀ. 72,403　　　　ሐ. 12,345

ለ. 49,402　　　　መ. 54,732

17. ከሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች ውስጥ **ብቸኛ ተጋማሽ** የሆነ ቁጥር የትኛው ነው ?

ሀ. 0　　　　ሐ. 2

ለ. 1　　　　መ. 3

18. ከሚከተሉት መካከል የ **648** ብቸኛ ትንትን የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. $2^3 \times 3^4$　　　　ሐ. $2^3 \times 3^2$

ለ. $2^3 \times 3^3$　　　　መ. $2^4 \times 3^4$

19. የ 424 እና የ **648 ትልቁ የጋራ አካፋይ** (ት.ጋ.አ) ስንት ነው ?

ሀ. 8　　　　ሐ. 5

ለ. 40　　　　መ. 36,040

20. ከሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች ውስጥ የ16 እና የ20 የጋራ ብዜት የቱ ነው ?

ሀ. 4　　　　ሐ. 40

ለ. 16　　　　መ. 80

LIVEWORKSHEETS

21.ከአንድ መናኸሪያ ሁለት የተለያዩ መስመር ያላቸው አውቶብሶች በተመሳሳይ ሰዓት ይነሳሉ፡፡ አንደኛው በየ12 ደቂቃ ቢነሳ ፤ ሁለተኛው በየ18 ደቂቃ ቢነሳ ፤ ሁለቱ አውቶብሶች እኩል አብረው የሚነሱት ከስንት ደቂቃ በኋላ ነው?

ሀ. 12 ሐ. 36

ለ. 18 መ. 2

22.የክፍልፋይ $\frac{105}{300}$ ዝቅተኛ ሂሳብ ቃል የቱ ነው ?

ሀ. $\frac{21}{60}$ ሐ. $\frac{7}{20}$

ለ. $\frac{35}{100}$ መ. $\frac{7}{12}$

23.አዲስ ከተጠየቀችው 60 ጥያቄዎች ውስጥ 40% በትክክል ብትመልስ በትክክል **የመለሰቻቸው ጥያቄዎች** ስንት ናቸው?

ሀ. 24 ሐ. 52

ለ. 36 መ. 60

24. ከሚከተሉት ውስጥ **0.054%** ወደ አስርዮሽ ሲቀየር የቱ ነው?

ሀ. 0.054 ሐ.0.54

ለ. 0.00054 መ. 5.4

25. ከሚከተሉት መካከል ከ**ትንሽ ወደ ትልቅ** በትክክል የተቀየረው የቱ ነው ?

ሀ. $0.7 < \frac{3}{4} < 1 < \frac{1}{2}$ ሐ. $1 < \frac{3}{4} < 0.7 < \frac{1}{2}$

ለ. $\frac{1}{2} < 1 < 0.7 < \frac{3}{4}$ መ. $\frac{1}{2} < 0.7 < \frac{3}{4} < 1$

LIVEWORKSHEETS

26. የ $\frac{15}{4}$ እና 1.25 ድምር ስንት ነው ?

ሀ. 2.5 ሐ. 5

ለ. 4.5 መ. 4

27. አቤል $13\frac{1}{5}$ ሜትር ርዝመት ያለው ገመድ ለሁለት ቆረጠው። የአንዱ ቁራጭ ርዝመት 6.85 ሜትር ቢሆን ሁለተኛው ቁራጭ ገመድ ምን ያክል ርዝመት አለው ?

ሀ. 4 ሐ. 4.5

ለ. 6.35 መ. 5

28. ከሚከተሉት መካከል ትክክል ያልሆነው የቱ ነው ?

ሀ. $2\frac{1}{4} \div 0.5 = \frac{9}{2}$ ሐ. $\frac{1}{9} \div 0.2 = \frac{5}{9}$

ለ. $3.25 \div \frac{2}{5} = \frac{65}{8}$ መ. $\frac{1}{5} \div 0.5 = \frac{1}{10}$

29. ከሚከተሉት መካከል የ$\frac{3}{4} \times 0.25$ ብዜት ውጤት የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. 18.75 ሐ. 0.1875

ለ. 187.5 መ. 1875

30.ሒሳባዊ ስሌት $2.12 \times 10^7$ በመቁጠሪያ ቁጥር ሲገለፅ የቱ ነው ?

ሀ. 2,120,000 ሐ. 2.120000000

ለ. 21,200,000 መ. 212

LIVEWORKSHEETS